# በግንቦት 20 የተበሰረ፣ በህገ መንግሥቱ የታሰረ ዴሞክራሲያዊ አንድነት

**ሠይፈ ደርቤ**

ያሳለፍናቸው 21 ዓመታት የልማትና የዴሞክራሲ ዓመታት ብቻ ነበሩን? ለመሆኑ ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፀደቀው ቻርተር ሀገራችንን እስከ 1987 ዓ/ም ድረስ እንዴት ይዟት ተጓዘ? ጣጠኛና ህዝብ አጫራሽ የተባለው ህገ መንግሥት ለኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የልማትና ዴሞክራሲ ጥማት ምን አበረከተ? በየዓመቱ የምናከብ ራቸው ግንቦቶች እነዚህን ጥያቄዎች የምንመልስባቸውና ወደ ኋላ መለስ ብለን የምናስተውላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

ሀገሪቱን ወደ ሞት ይዟት እየተጓዘ ነው የተባለው የመንግሥት ፖሊሲ ገደለን ወይስ እመርታ ካሳዩ ሀገሮች ተርታ አሰለፈን? የማያባራ መቅሰፍት ይወርድባታል የተባለችው ሀገር ምን ደረጃ ላይ ደረሰች?… ሌሎች ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው ሟርቶች በሱባኤ ወይስ በተጋፍጦ ታለፉ?

አሁንም የግንቦት 20 ድል 21ኛ ዓመት ዓላማ ግብ ማምታት አለመምታቱን በትክክል መመዘን የምንችለው ይህን በተገቢው ስንመ ረምር ነው፡፡… ውድ አንባቢያን <<እንኳን የራሳችሁ የነፃነት፣ የእኩልነት፣ የልማትና ዴሞክራሲ በዓል አደረሳችሁ!>>

ኢትዮጵያ ያለ ብሔር ብሔረሰቦቿ ኢትዮጵያ አይደለችም፤ ብሔሮቿን ያላገናዘበ ኢትዮጵያዊነት ከእርስ በእርስ ጦርነት፣ እልቂትና መበታተን ሊያድናት አይችልም፡፡ በሀገራችን የተለያዩ ክልሎች የተካሄዱ አመፆችን ጨምሮ የ17 ዓመታቱ መራር ጦርነት የዚህ ገለፃ ማሳያ ይሆናል፡፡

የባሌ አርሶ አደሮች አመፅ፣ የትግራይ አርሶ አደሮች አመፅ፣ የጎጃም አርሶ አደሮች አመፅ ወዘተ… እየተባሉ ሲጠቀሱ የምንሰማ ቸው የትግል ታሪኮች የኢትዮጵያ ብሔሮች የብሔርና የመደብ ጭቆናዎች ምን ያህል እንዳንገሸገሿቸው የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ልትጠፋና ልትበታተን ነው ተብሎ ህልቆ መሳፍርት የሌለው ሟርት ሲነገር የነበረው የኢፌዴሪ ህገ መንግሥት በያዛቸው ድንጋጌዎች በተለይም በአንቀፅ 39 ጉዳይ ነው፤ አንቀፅ 39ን <<ጣጠኛው አንቀፅ>> ብለው ከሚገልፁ ወገኖች ጀምሮ <<ገና ሳይፀድቅ ህዝብ ማባላቱን ጀመረ፣ የአንዱን እምነት ተከታይ በሌላው ላይ አስነሳ፣ ኢትዮጵያ አለቀላት፣ የማያቋርጥ መቅሰፍት ሊወርድባት ነው>> የሚሉ አሸባሪ ወሬዎችን የፕሬስ ነፃነቱን ተከትለው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ አሸን የፈሉት የግል ህትመቶች ተቀባብለውታል፡፡

እነዚሁ ጋዜጦች በሚያወጧቸው የሽብር ወሬዎች ብቻ ሳይሆን በመጠሪያ ስማቸውም ርዕድ የሚፈጥሩ ነበሩ፤ ገሞራ፣ ሰይፈ ነበልባል፣ ማዕበል፣ ተናገር፣ ጦማር፣ ጦቢያ፣ ኢትኦጵ፣ ኡርጂ ወዘተ… ከጋዜጦቹ በተለይ የአሸባሪውን አካባ አቋም ይዘውና የቡድኑ ልሳን ሆነው የሚያዋጉም ይገኙበታል፡፡

<<አካባ ወያኔና ሻዕቢያን ከግዛቱ ሊሞላ ልጫቸው ማለ፣ ኢትዮጵያ ለከባዱ ጦርነት ተዘጋጅታለች፣ አካባና አዕካባ በ…አካባቢ ድል ቀንቷቸዋል…>> የሚሉ ወሬዎች የዕለት ተዕለት ስጋት ሆነዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያከተመ ለመሆኑ በዚህ መልኩ የሚሰራጩ የፈጠራ ወሬዎች የየሳምንቱ መርዶ ነጋሪዎች ነበ፡፡

የአንቀፅ 39 ጉዳይ ህማም የሆነባቸው በስም የአንድ ኢትዮጵያ ናፋቂዎች ስለ ህዝባቸውና ስለ ሀገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ ሳያጤኑ የሚሰጧቸው አስተያየቶችን ጨምሮ አንዳንድ ጎረቤት ሀገሮች የኢትዮጵያ ተሞክሮ ወደ እኛም ይዛመታል የሚል ስጋት ነበራ ቸው፡፡ እነዚሁ ጎረቤት ሀገሮች ውስጣቸው በምን እንደሚታመስ ቢያውቁም ጉዳዩን በዝምታ አፍነውት ቆይተዋል፤ ወደ ኋላ ላይም መፍትሄው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልን ድረስ መሆኑን ተገንዝበው ኢትዮጵያን በአርአያነት ተከት ለዋል፡፡ ይሁንና በወቅቱ አስተምህሮቱን አደገኛና ከፋፋይ ሲሉ ተችተዋል፡፡

የኢት ዮጵያ መበታተን አይቀሬ መሆኑንም ገልጸ ዋል፡፡

አዲሱ ሥርዓት በመላው ሀገሪቱ የተንሰ ራፋውን ልክ የሌለው ድህነት የማስወገድ የቤት ስራን ጨምሮ ከዚህም ከዚያም የሚወረወረውን የፖለቲካ ጣጣ የማርገብ ኃላፊነት ተቀብሏል፡፡ ከጦረኝነቱ አባዜ ላለመውጣት የቆረጡትን እነ አነግ እንዲሁም አለመረጋጋቱ ባስከተለው ጦስ ደርግ በረጨው የጦር መሳሪያ ራሳቸውን ያደራጁ ሽፍቶች በተለያዩ ክልሎች የሚፈፅሟቸውን ግድያና ወከባዎች ተከታትሎ የማክሰም ልዩ ኃላፊነትም የሽግግሩ መንግሥት ነበር፡፡

ይህን ዛሬ ላይ ሆነን ስናስብ የሥርዓቱ ጉዞ አልጋ በአልጋ ያልነበረ ብቻ ሳይሆን ፀረ ልማትና ፀረ ዴሞክራሲን በብርቱ የመዋጋት ከፍተኛ ኃላፊነት እንደነበረበት እንገነዘባለን፡፡ ሥርዓቱ እነዚህኑ ችግሮች ለማሸነፍ ህገ መንግሥቱ ትልቅ አቅም እንደሆነውም እንረዳለን፡፡በአንቀፅ 39 ላይ የሰፈረው የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ገደብ የሌለው መብትን ጨምሮ የህገ መንግሥቱ ምሰሶዎች ተብለው የሚታመኑት ከአንቀፅ 8 እስከ አንቀፅ 12 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ሀገራችን ዛሬ ለደረሰችበት ሁለንተናዊ ስኬት መሰረቶች ናቸው፡፡

የህዝብ ሉዓላዊነት፣ የህገ መንግሥት የበላይነት፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ የመንግሥትና የኃይማኖት መለያየት፣ የመንግሥት የአሰራር ተጠያቂነት ጉዳይ በምን መልኩ ተግባራዊ እንደሚሆን በህገ መንግሥቱ በግልፅ ሰፍሯል፤ ይኸው መብቶቹ ሳይሸራረፉ እንዲጓዙ መንግሥት ለራሱ አብዝቶ የሰጠውን የቤት ሥራ እንድንመለከት ያደርገናል፡፡

በአንቀፅ 40 እና 41 ላይ የተደነገጉት የንብረት፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች የኢትዮጵያ ብሔሮች የእኩል ተጠቃሚነት መሰረቶች ናቸው፡፡ ሀገራችንን ለከፍተኛ እመርታ ያበቁ የየዘርፉ ፖሊሲዎችም «በሟርተኞች ይበታተናል፣ ያጠፋል» ሲባል ከነበረው ህገ መንግሥትና ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት የመነጩ ናቸው፡፡

እነዚህን መብቶች ለማግኘት ባስቻለው እልህ አስጨራሽ ትግል በብሔራችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ድርብ ጭቆናና የመደብ ጭቆና መወገድ አለበት ያሉ የህዝብ ልጆች ህይወታቸውን፣ አካላቸውንና ወጣትነታቸውን ከፍለዋል፡፡መስዋዕትነታቸው በታገሉለት ዓላማ ግብ መምታት ህያው ሆኖ እንዲቀርና የህዝብ የልማትና የዴሞክራሲ ጥማት እንዲረካ የቃላቸውን አሻራ በህገ መንግሥቱ ሰነድ አትመዋል፤ በሀገሪቱ ዳግም ጭቆና ላይነግስ፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነታቸውና እኩል ተጠቃሚነታቸው ሊረጋገጥ፣ ሉዓላዊነታቸው ላይሸራረፍ ህገ መንግሥታዊ ሰነዱ ዋስትና ሆኗል፡፡ የእዚህ እውነታና ቃል ኪዳን ማብሰሪያ ግንቦት 20፣ የቃል ኪዳኑ ማሰሪያ ደግሞ ህገ መንግሥቱ ነው፡፡

ግንቦት 20 የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረ ሰቦችና ህዝቦች የፀረ ጭቆና ተጋድሎ በውጤት የተደመደመበት ልዩ ዕለት ነው፤ ዕለቱ የድህነቱ ዘበኛ ተወግዶ ህዝቦች ከብቸኛ ጠላታቸው ድህነት ጋር ግብግብ እንዲገጥሙ እድል ሰጥቷል፡፡ በግንቦት 20ው ድል በመሬት ላይ ከተመሰረተ የኃይል አንድነት፣ በህዝቦች ላይ ወደ ተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ተሸጋግረናል፡፡ ተከባብረን መኖር ካልቻልን ተለያይተን በሰላም መኖር እንድንችል ዋስትና አግኝተናል፡፡ የትኛውም ልዩነት ያለ ደም መፋሰስ የሚፈታበት አዲስ የሥልጣኔና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ካስማ ተክለናል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራ ሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ግንቦት 83 ዓ/ም የደርግ ሥርዓት ማክተሙን በማብሰር ህዝቦች ወደ አዲስ

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገ ራቸውን በይፋ ሲያውጅ ሀገሪቱ በበርካታ ውጣ ውረድና ውዥንብሮች መዳፍ ስር ነበረች፡፡ዛሬ ሀገራችን የደረሰችበት አጠቃላይ እድገት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ችግሩን በፅናት በማለፍ የተገኘ ነው፡፡ በርካቶች ውድ ህይወታቸውን ሰውተው እኛ እንድንኖር ስላደረጉንም ነው፡፡ የድህነቱ ዘበኛ ደርግን ስላስወገዱልንም ጭምር ነው፡፡ዛሬ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ኃያልና ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሰኘት የበቃችው የራሷን የቤት ስራ በተገቢው በማከናወኗ ነው፡፡ ለውስጥ ጉዳይዋ ትኩረት ሰጥታ አንገት ያስደፋትን ድህነት ማራድና መነቅነቅ በመጀመሯ ነው፡፡

በግንቦት 20 ማግስት አገሪቱ አለቀላት ብለው ያሟረቱ ወገኖች የሀገሪቱ ስጋት ረሃብ ብቻ ሳይሆን የሰላም እጦት እንደነበር ሲገልፁ ተስተውሏል፡፡ አርሶ አደርነትን እንዳለመሰ ልጠን ቆጥረውና በትምክህት ሠራዊታችንን ገበሬ ሠራዊት ብለው በመዝለፍ ለዚህ ልዩ እለት ላደረሰን አርሶ አደር ያላቸውን ንቀትም ገልፀዋል፡፡

ያኔም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሆነችው፣ ኢትዮጵያም ሆና የምትቀጥለው፣ የሥልጣኔዋና የእድገቷም ምንጭ ገበሬው ያለመሆኑን ከቶም ያልተገነዘቡት ሟርተኞቹ በአርሶ አደሩ ትጋት የተለወጠችው ሀገር በአፍሪካና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ተፅዕኖ ስትፈጥር ቁጭ ብለው መመልከት ጀምረዋል፡፡ገበሬው ሠራዊት ከራሱ አልፎ የአካባቢው ሀገራትና የአህጉሩ ኩራት መሆኑን አይተዋል፡፡ በሁለት ተቀናቃኝ ሀገሮች በእኩል የሚፈለግ፣ ታማኝና ዲሲፕሊን ያለው ጀግና ሠራዊት መሆኑን አስተውለዋል፤ በዘለፋቸውም ልክ አፍረዋል፡፡

ሠራዊታችን ሩዋንዳ ሲዘምት አይሳካለትም ተዋርዶ ይመለሳል እንዳሉ፣ ሩዋንዳውያን <ሰላማችንን ስላስከበርክልን፣ ከጭፍጨፋ ስለታደግከን እናስታውስሃለን፣ እናከብርሃለን> ብለው ሲሸልሙትና ሀገራችንን ሲያኮሩ ለማየት ተገድደዋል፡፡ በላይቤሪያ፣ ብሩንዲ፣ ሶማሊያና ሱዳን እየሆነ ያለውና የሆነው ይኸው ነው፡፡ ሀገራችንን ለዘመናት ውርደት ዳርጓት የቆየው ረሃብ ዜጎቻችን በሀገር ውስጥም በውጭም ቀና ብለው እንዳይሄዱ እንዳላደ ረገው ሁሉ በህዝቡ የልማት ትግል እየተሸነፈ ያለው ግንቦት 20 በፈጠረው ዴሞክራሲያዊ አንድነትና ሰላምም ነው፡፡ ለፀረ ድህነት ትግሉ መሰረት በሆነው የልማት ፖሊሲ የተከናወኑ ተግባራት ረሃብ እንዳይከሰት አድርገው ድርቅን እንድንቋቋም አስችለውናል፡፡

ይህን አርአያነት ያለው ተግባር ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችና የድርቅ ተጎጂዎች ከኢትዮጵያ ይማሩ እያሉ ያሉት የመንግሥታቱ ድርጅትና ዓለም ባንክ ሰዎች መሆናቸው ሲታሰብ መንግሥታችን ከትግሉ ዋዜማ ጀምሮ አሁን በተጨባጭ እያከናወነ ባለው አጠቃላይ ልማት ይዞት የተነሳው ፖሊሲ፣ በጣልቃ ገቦች ያለመጠምዘዝ ብርታትና ያለመሸነፍ ፅናት የግንቦት 20ን ድል ያጎሉታል፡፡ የግንቦት 20 ድል ዓላማና ግቦች መሳካት መጀመሩንም ያሳያል።

በዚህ ጥምረትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት የተጀመረው ትስስር ድህነትን ለማሸነፍ የሚደረገው ትግል በተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት እንዲጠናከር፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበ ካሉ ሀገሮች ተርታ እንድንሰለፍም አስችሎናል።ወደ ብልፅግና ለማምራት በተያያዝነው መንገድ የልማትና የዴሞክራሲ አንድነታችን ምንጭ በሆነው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የጋራ አጀንዳ ሥር ተሰባስበን ለሀገራችን በእኩል እንድንታትር አድርጐናል።

ለዘጠኝ ዓመታት በተከታታይ የተመዘገበው እድገት ወገብን ወደሚፈትሸው ሀገራዊ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ክንውን እንድናመራ አቅጣጫ አመላክቶናል። እነሆ በእቅዱ የአንድ ዓመቱን ጉዞ አጠናቅቀን ሁለተኛውን ምዕራፍ ተያይዘናል፤ ይህ የሆነው በግንቦት 20 በተበሰረው ድልና በህገመንግሥቱ ቃልኪዳን በፅናት መጓዝ በመቻላችን ነው።